ቁሳቁሶችን መመደብ

- ቁሳቁሶች በሁለት ይመደባሉ።እነሱም ፡-የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች ናቸው።

➢ **የተፈጥሮ ቁሳቁሶች** የሚባሉት በተፈጥሮ የሚገኙ ቁሳቁሶች ናቸው።

ምሳሌ፡- ድንጋይ፣እንጨት፣ጥጥ፣ገለባ፣ሱፍ

➢ **ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች**፡-ለተለያዩ ተግባራት ይውላሉ።ምሳሌ፡-ፕላስቲክ፣ብርጭቆ

የተፈጥሮ ሀብቶች

- የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት በተፈጥሮ የሚገኙና ሰዎች ጥቅም ላይ የሚያዉሏቸው ሀብቶች ናቸው።ምሳሌ፡-አፈር፣ውሀ፣እፅዋት፣አየር፣እንስሳት

የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅም

- **ተክሎች**–ለአልባሳት መስሪያነት፣ለእንስሳት መጠለያነት፣ለመድሀኒት መስሪያነት ይጠቅማሉ።
- ማዕድናት (ወርቅ፣ነዳጅ፣ጨው ና የመሳሰሉት):ለሀይል ምንጭ ነት፣ለመድሀኒት፣ለቤት ግንባታና ለመሳሰሉት ይጠቅማሉ።
- ተፈጥሮአዊ የቱሪስት መስህቦች:-የሚባሉት ማራኪና ልዩ ልዩ ገፅታ ያላቸው የአንድ አካባቢ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው።

ምሳሌ :- የውሀ ፏፏቴ፣ብርቅየ እንስሳት፣ሀይቆችና ፍልውሀዎች

የአፈር መሸርሸር (መከላት)

- ጎርፍ፣ንፋስና የደን መጨፍጨፍ የአፈር መከላት መንስኤዎች ናቸው።
- የደን ጥበቃ ማለት ዛፎችን ያለ በቂ ምክንያት አለመቁረጥ፣አለመጨፍጨፍና አለማቃጠል ማለት ነው።

በዙሪያችን የሚገኙ ተክሎች

የተክሎች ክፍሎች

✓ ግንድ ፣ቅጠል ፣አበባና ስር ናቸው።

የተክሎች ክፍሎች ተግባር

- **ግንድ** :- የተክሎችን ቅጠሎችና ቅርንጫፎች ይሸከማል።

  - ውሀና ማዕድናትን ወደ ቅጠሎችና ቅርንጫፎች ያደርሳሉ።

- **ቅጠል** :- ዋና ተግባሩ ምግብን ማዘጋጀት ሲሆን ቅጠሎች በመጠናቸው ፣በቅርፃቸውና በጠርዛቻቸው ይለያያሉ።
- **አበባ** :- ተክሎች እንዲራቡ ያደርጋል።ዘር እና ፍሬ የሚፈጠርበት የተክል ክፍል ነው።
- **ስር** :- ውሀና ሟሚ ማዕድናትን ወደ ግንድ ያስተላልፋል።

እንስሳት

- እንስሳት በአረባባቸው፣በእንቅስቃሴያቸው፣በአመጋገባቸው፣በመኖሪያ ስፍራቸውና በሰውነት ሽፋናቸው መሰረት ይመደባሉ።
- እንስሳት በአረባባቸው መሰረት በሁለት ይመደባሉ።እነሱም ፡-ልጅ የሚወልዱና እንቁላል የሚጥሉ ናቸው።
- ✓ **ልጅየሚወልዱ ፡ምሰሌ ፡-**ላም፣አንበሳ፣ድመት፣ጅብ
- ✓ **እነቁላል የሚጥሉ ፡**ምሳሌ፡-ዶሮ፣ወፍ፣እባብ
- በእንቅስቃሴያቸው መሰረት በሰማይ የሚበሩ፣በመሬት ላይ የሚሳቡ፣በእግራቸው የሚራመዱና በውሃ ውስጥ የሚዋኙ ተብለው ይመደባሉ።
- **በአመጋገባቸው መሰረት በሶስት ይመደባሉ።**

1.ስጋ በል እንስሳት ፡-ምሳሌ አንበሳ፣ውሻ፣ነብር

2.እፅዋት በል ፡-ምሳሌ ላም፣ፍየል፣ግመል፣ቀጭኔ

3.ስጋና እፅዋት በል ፡-ምሳሌ ሰው፣አይጥ፣ዝንጀሮ

- **በመኖሪያ ስፍራቸው መሰረት፡**በመሬት፣በውሀና በመሬትም በውሃ ውስጥ የሚኖሩ ተብለው ይመደባሉ።
- **በሰውነት ሽፋናቸው መሰረት ደግሞ በ *3*ይመደባሉ።**

1.በላባ የተሸፈነ:-ምሳሌ:ዶሮ፣ወፍ፣ቆቅ፣አሞራ

2.በፀጉር የተሸፈነ :-ምሳሌ:ላም፣ውሻ፣ዝሆን

3.በቅርፊት የተሸፈነ:-ምሳሌ:-እባብ፣እንሽላሊት፣አዞ፣አሳ

- እንስሳት ለምግብነት፣ልብስ ለመስራት፣ለጉልበት ስራና ለጥበቃ ይጠቅማሉ።

አዘጋጅ ፡-መ/ር አህመድ